

# የሴት ልጅ ግርዘት፣
# ለዘልዓለም መወገድ ያለበት ልምድ ነው

የሚኒስቴሮች ምክር ቤት
የእኩል ዕድሎች ሚኒስቴር

# የሴት ልጅ ግርዛት፣
# ለዘልዓለም መወገድ ያለበት ልምድ ነው

## የተከበራቹ ወላጆች

የሴት ልጅ ግርዘት፣ በመላው ኣህጉር፣ በኣፍሪቃ ኣህጉር ጭምር የተኮነነ፣ በማንኛውም ሃይማኖ የማይፈቀድና ጊዜ ያለፈበት የጭካኔና ኢሰብኣዊ ድርጊት ነው።
ይሂ ዓረመኔ ድርጊት የተፈጸመባት ሴት ለመላ ሕይወትዋ የማይድን መንፈሰ-ኣካላዊ ቁስል ያስከትልባታል።
ኣንዷት ሕጻን ምግረዝ በጤናዋ ላይ ከባድ ጉዳትና ኣደጋ እንደሚያደርስባትና ወላጆች ብሃገራችንም ሆኔ በሌላ የኤሮጳ ኣህጉር ውስጥ ከባድ ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው መገንዘብ ኣስፈላጊ ነው።
ወላጆች ልጆቻቸውን በሕግ በሚያስቀጣው ተግባር ለመዳረግ ግዴታ፣ ወይም ጥቅም እንደሌለ ማወቅ ይኖርባቸዋል።
ብዙ ሕዝቦች ለመን ይህንን ልምድ እንደሚያዘወትሩ ግልጽ ኣይደለም።

የጥንት ልማዱ ለምን እንደሚያደርጉት ሳይጠይቁ በጭፍን ተቀብለው እንደሚያዘወትሩት ይገመታል።
መነሻው በግብጽ ፈርዖኖች ዘመን መሆኑን ይተረካል።
ከዛ ጊዜ ጀምሮ የተለያየ መልክ ይዞ በመላው የኣፍሪቃ ኣህጉር ተስፋፋ።
በሃገራችን ለመኖር የመረጡት የውጭ ዜጎች ከሕብረተሰቡ የበለጠ ለመወሃሃድ የሚችሉበት መንገድ በመወያየትና ዕውቀት በመከማቸት መሆኑን እናምናለን።



ስለዚህም ኢጣልያና ሌሎች ዓለም ዓቅፍ ማሕበሬሰቦች፡ ስነኣእምሮኣዊና ኣካላዊ ሙሉነት ጨምሮ መጣስ የሌለባቸው መብቶች እንዳሉ በዚህ በራሪ ጽሑፍ መግለለጽ እንዳለብን እናምናለን።
ጥንታዊ የሆነ ባሕልና ልምድ ለመተው ኣስቸጋሪ መሆኑን ይገባናል፡ ነገርግን ከጥንቆላ በተያያዜ ድርጊት ለኣካላዊና መንፈሳዊ ጉዳት የተጋለጡትን ልጆቻችሁ ለጤንነታቸውና ደስታቸው ማሰብ እንዳለባችሁ እናምናለን።
ሴት ልጆጃችሁ በኣዲሱ ክፍለዘመን እንደጣልያን ዜጎች በጣልያን ኣገር ይኖራሉ።
ስለዚህ መጪውን ጊዜ በተስፋና በፈገግታ እንጊጋፈጡት እንርዳቸው።

የእኩል ዕድሎች ምኒስቴር



# የሴት ልጅ የብልት ኣፍ ለመስፋት የሚቀርቡትን ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም

የሴት ልጅ ግርዘት ምክንያታዊ ለማድረግ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እርስ በርሳቸው የሚገራጩ የተልያዩ ምክንያቶች ይቀርቡ ነበር።
ከሕዝብ ወደ ሕዝብና በጂኦግራፊያዊ ክልል ትንሽ ቢለያዩም ሁሉም በሃይማኖታዊ ወይንም በጥንቆላዊና ባህላዊ እምነት የተመሰረቱ ናቸው።
ባብዛኛው ጊዜ የሚከተሉትን እንደ ምክንያት ይቀርባሉ፥

## 1. ሃይማኖታዊ ልምድ

መጽሕፍ ቅዱስ ሆነ ቁርኣን የሴት ልጅ ግርዘት ኣያዙም። በብዙ ሃይማኖቶች መካከል በዚሁ ልምድ እምነት ተራ እንደሌለው ለማሳየት ብዙ ኣስተሳሰቦች በየጊዜው ተነስተዋል።

## 2. ባህል ለመጠበቅ

ባሕል ኣንድ ኮሙዩኒቲ ቀጣይ ከሆነ ማሕበራዊና ታሪካዊ እድገቶች የሚያዳብረው ልምድ ነው። የሄም ለሴት ልጅ ግርዘት ይመለከታል።
ልምዱን መተው ማለት ሴት ልጅ ባህልዋን ካደች ማለት ኣይደለም፥ ባንጻርሩ ከኣዲስ ክብሮች እንደ ሰብኣዊ መብቶችና የሴቶች የምርጫ ነጻነት የመሳስሉትን ኣዳዲስ ክብሮች ጋር ትስስር ትፈጥራለች እንጂ።



**3. ኣስፈላጊ የሆነ የኣነሳሺነት ስነስርዓት ነው።**

ወደ ጉርምስና የመሸጋገርያ ስነስርዓት በብዙ ቦታዎች እየቀረ ነው። ደም ሳይፈስ የሚደረጉ በዓላትና ድግሶች፡ ወደጉርምስና የምትሸጋገርበት ወቅት በሰላማዊ መንገድ ማሕበራዊ ዕውቅና ያረጋግጥላታል።

**4. ንጽሕና ይጠብቃል**

በተቃራኒው በዘር ኣካሎችና በሽንት ኣካሎች ላይ የቁስል ማመርቀዝ ያስከተላል። ጽዳት ለመጠበቅ ካስፈለገ መድሃኒቱ በተከታታይ መታጠብ ነው።

**5. ለውበት የጠቅማል እየተባለ የሚቀርብ ምክንያት**

የሴት ልጅ ብልት ጠፍጣፋ መሆን ኣለበት የሚለው ኣስተሳሰብ በእውነታ ምንም ማረጋገጫ ኣልተገኘለትም።

**6. የሴት ብልት መስፋት ድንግልናን ለመጠበቅ ያግዛል የሚለው ኣስተሳሰብ**

ትክክል ኣይደለም። ምክንያቱም ከግብረስጋዊ ግኑኙነት በውሃላ እንደገና ይሰፋል። ይልቁንስ የሚቀሰመው ትምህርታና ግላዊ ክብሮች ናቸው ለግብረስጋዊ ምርጫዎች የሚመሩን።

**7. የባህል ወሲባዊ ፍላጎት እንዲጨምር ይረዳል የሚለው ኣስተሳሰብ**

እውነት ኣይደለም ምክንያቱም የወንዶች ወሲባዊ ፍላጎት ከሴቶች አኩል የሆነ ግብረመልስ ሲያገኝ ሊጨምር እንደሚችል ተረጋግጠዋል። ባንጻሩ ወሲባዊ ግኑኙነት ለሰቶች ባጣም ኣሳማሚ ነው የሚሆንባቸው እንዲሁም ወንዶች ብልታቸው ብሴት ብልት ማስገባት ኣስቸጋሪ ነው የሚሆንባቸው።

**8. ሞራላዊ ካልሆነ ወሲባዊ ባርይ ይከላከላል የሚለውን ኣስተሳሰብ**

ትክክል ኣይደለም ምክንያቱም ሲቶችን ሕገወጥ በሆኑ ልምዶች እንዳይሳተፉ ኣያስቆማቸውም።

## የሴቶች ግርዘት ምን ማለታችን ነው።

የተለያዩ ሴት ልጅ የግርዘት ኣገባቦች ኣሉ፣ ሁሉም ጎጂ ሲሆኑ እንደሚከተለው ይከፋፈላሉ፣

የሱና ግርዘት። ይሄኛው ዓይነት በሴት ቅንጢር የሚፈጸም ነው።

ቅንጢር መቁረጥ። እዚህ ላይ ቅንጢሩ በሙሉ ይቆረጣል።

ብልት መስፋት። ለሽንትና ለወር ኣበባ ፈሳሽ መውጫ የሚሆን ትንሽ ቀዳዳ ተትቶ የብልት ኣፍ በሙሉ ይሰፋል።

ከተጠቀሱት ውጪ በግልጽ ተለይተው ያልታወቁት ሌሎች ልምዶችም ኣሉ። ሁሉም በሴት ብልት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ናቸው።



# በሴ ልጅ ጤና ላይ ያለው ጠንቅ

የተከበራችሁ ወላጆች ይሂ ልምድ በሴት ልጆቻችሁ ስነኣእምሮኣዊና ኣካላዊ ጤና ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ከባድ መሆኑን መገንዘብ ኣለባችሁ። የግርዘቱ ዓይነት ሆኔ ፈጻሚው ሰው እንዲሁም የተፈጸመበት የጽዳት ሁኔታ ሳይለይ በሴት ልጆቻችሁ ሂወት ላይ ምንጊዜም ጉዳትና ውርደት የሚያደርስ ነው። ባንዳንድ ወቅትም እስከመሞት ሊያደርስ ይችላል።

በመጀመርያ ማንኛውም የብልት መስፋት ዓይነት ተራ በልምድ የሚደረግ ቀዶ ጥገና ሳይሆን ከባድና ችሎታ የሚጠይቅ የኣካለ ፍሬ ቀዶ ጥገና ነው።
በሆስፒታል ውስጥ በባሌሙያዎች ያልተደረገ የኣካለ ፍሬ ቀዶ ጥገና የታካሚውን ሂወት ኣደጋ ላይ ነው የሚጥለው።

ይሂ የመቆራረጡ ድርጊት ካለማደንዘዣና የቀዶ ጥገና ዋስትና ከተፈጸመ በቁስሉና በመድማት ምክንያት የሚደርሰው ከባድ ሕመም ምክንያት ኣብዛኛው ጊዜ ሴቶች ኣእምሮዋቸውን ይስታሉ።
መድማት በዚሁ ቀዶ ጥገና ምክንያት የሚደርስ የማይቀር ኣብዛኛው ጊዜ እስከሞት የሚያደርስ ጥንቅ ነው።
በእርግጥ ቅንጢር በሰውነት የደም ስሮች ከሚበዙበት ኣካሎች ኣንዱ ነው፡ የመድማቱ ሂደት ተሎ እንዲቆም ካልተደረገ ልጅትዋ ልትሞት ትችላለች።
እንዲሁም መድማቱ ከባድ ባይሆንም፡ ደም ለቀናት ስለሚፈስባት ከባድ የደም ማነስ ችግር ሊያስከትልባት ይችላል።

ነገር ግን የኣጭር ጊዜ ኣደጋዎች ብቻ ኣይደሉም ያሉት። ምንም እንኳን መድማቱ ቢያቆምም፡ ገና የቁስሉ የመመርቀዝ ኣደጋ ኣለ።

መመርቀዝ የሚመጣው ጽዳቱ ያልተጠበቀ ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ምክንያት ነው። ከቀዶ ጥገናው በውሃላ ሕመሙ በአጭር ጊዜ አይታገስም።
ሴቶቹ ለቀናት ሽንት መሽናት እስከሚያቆሙበት ደረጃ ድረስ ነው በሕመሙ ምክንያት የሚሰቃዩት።
ያለመሽናቱ ደግም ሌላ ራሱ የቻለ የሽንት ምቋጠር ችግር ያስከትላል።
በዚሁ ምክንያት ደግሞ የሽንት አካላት ይመረቅዛሉ በሴትዋ ላይም ሌላ ተጨማሪ የጤና ችግር ይፈጥራል።
ምርቀዛው ባካባቢው ካሉት አካላት እንዴ የሽንት ቱቦ፣ እምስና፣ ቂጥ በመሰሉ አካሎች ይስፋፋል።



ከተለመደው የመመርቀዝ ሁኔታ ውጪ ንጽሕናው ያልተጠበቀ መሳርያ በመጠቀም ምክንያት ሴትዋ በተታኍስ በኤይድስ ወይንም ከጉብት በሽታ ምክንያት ልትሞት እንደምትችል መገንዘብ ይኖርባቹሃል።

ልጅትዋ ቀዶ ጥገናው የሚያደርሰውን ችግሮች ተቋቁማ ለመኖር ከቻለች ደግሞ ካደገች በውሃላ በተለያዩ ቀዋሚ ጉዳቶችና በሽታዎች ትሰቃያለች። አነዚህ ችግሮች ደስተኛ ኑሮ እንዳትኖር ይከለክሉዋታል እንዲሁም ለዕድሜዋ ማጠር ምክንያት ይሆናሉ።

ከነዚሁ መሃከል በተደጋጋሚ የሚታዩት፣
ለመሽናት መቸገር፣ የሽንት ቱቦ በመዘጋት ወይምን የሽንት መተላለፊያ አካል በመጎዳቱ ምክንያት ሊደርስ ይችላል።
መሽናት በጣም አሳማሚ ይሆናል። በዚሁ ምክንያት የተነሳ ደግሞ ሰቶች በተቻላቸው መጠን ትንሽ ሽንት ለመሽናት ይገደዳሉ። የሂ ሁኔታ ከመመርቀዝ ጋር የተያያዜ የሽንት አካሎች የመታመም ችግር ያስከትላል።



ስር የሰደደ ቀጣይና ደጋግሞ የሚመጣ የእምስና የፍሬ አካሎች መመርቀዝ።

ልጆች መውለድ አለመቻል (መካንነት)፣ ባጠቃላይ በመመርቀዝ ምክንያት በዘር አካላት ሊጠገን የማይችል ጉዳት ሲደርስባቸው ሊሆን ይችላል።

በእምስ ከንፈር ጠባሳ ማስከተል፣ ጠባሳው እምሱ እንዲጠብ ያደርገዋል ወሲብ መፈፀም አስቸጋሪ እስከሚሆንበት ድረስ ይሆናል እንዲሁም የወር አበባ ደም በደንብ ወደ ውጭ እንዳይፈስ ይሆናል።

በእምስና በፊኛ ወይንም በእምስና በቂጥ መካከል ቀዳዳ መፍጠር።

በዙሁ ሁኔታ ሽንትና ኣር ኣብሮ ተቀላቅሎ ይወጣል።

ይህቺ ያልታደለችው ሴት ወሲብ ኣሳማሚ መሆን የማይቀረው ዕጣ ፋንታዋ ነው። ኣንዳንድ ጊዜ በወሲብ ጊዜ የወንድ ብልት በጭራስ ኣልገባም ባይለም ወደ ውስጥ መግባቱ ኣስቸጋሪ ይሆናል። ኣንዳንድ ጊዜም ወሲብ ለመፍጸም ቀዶጥገና የሚያስፈልግበት ወቅት ኣለ።

ነገር ግን እነዚህ የተገረዙት ሴቶች የተጠቀሱት ኣደጋዎችና ችግሮች ኣልፈው ማርገዝ ከቻሉ፡ በጽንስና በወሊድ ጊዜ ሌላ ችግሮች ያጋጥማቸዋል። የግርዘት ችግር በደረሰባቸው ሴቶች ይሄ ችግር የተለመደ ነው። ጠባሳው የወሊድ መተላለፍያ መንገድ በደንብ እንዳይለጠጥ ያደርገዋል ሕጻኑም እንዳይወለድ ያግደዋል።
ከዚህ ሌላ ደግሞ ሌሎች የተለያዩ እበጦች ይፈጥራል። ኣንዳንድ ጊዜም የነርቭ ክምችት ያለበት ዕጢ ይፈጥርና ባጠቃላይ ኣካባቢው ሓይለኛ ስሜት እንዲኖረው ይሆናል ለመቋቋሙ ኣስቸጋሪ የሆነ ሕመምም ያስከትላል።



# በጣልያን ኣገር በኣንዲት ሴት ልጅ ብልት ላይ ጉዳት ማድረስ ምን ልያስከትል ይችላል

በቅርቡ ፓርላማ፤ ሴት ልጅ መግረዝ ወንጀል መሆኑን የሚገልጽ ህግ ኣጽድቀዋል።

በተለይ የሴት ልጅ መገረዝን የሚጎተጉቱ ሰዎች ከኣራት እስከ ኣስራሁለት ኣመት የሚደርስ እስራት ያስከትልባቸዋል።

የሴት ልጅ ግርዘት፤ ቅንጢር መቁረጥ፡ የብልት ከንፈር መቁረጥ፡ የብልት ኣፍ ማጥበብና እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶች ያጠቃልላል።



ከላይ ከተጠቀሱት በስተቀር፤ ሌሎች በሴት ልጅ ብልት ጉዳት ማድረስ እንዲሁም ስጋዊና መንፈሳዊ ህመም ወይንም ጉዳት ማድረስ ከሶስት እስከ ሰባት ኣመት እስራት ያስከትላል። ጉዳቱ ቀላል ከሆነ ፍርዱ በኣንድ ሶስተኛ ይቀንሳል።

እነዚህ ድርጊቶች በህጻናት ጉዳት ካደረሱ ወይንም ድርጊቶቹ ትርፍ ለማግኘት የተፈጸሙ ከሆነ ቅጣቱ በኣንድ ሶስተኛ ከፍ ይላል።

እንደዚሁ ኣይነት ድርጊቶች ከኣገር ውጪ በሚኖሩ የጣልያን ዜጎች ወይንም በኣገር ውስጥ የሚኖሩ የውጪ ዜጎች የተፈጸሙ ከሆነ ኣንቀጾቹ ተግባራዊ ይሆናሉ።



## ማጠቃለያ

የብልት ኣፍ መስፋት እንደሌሎቹ የብልት መቆራረጥ በልጆቻችሁ ላይ ጉዳት ያደርሳል።
እነዚህ ልምዶች የዓለም የጤና ድርጅት ጨምሮ የተለያዩ የዓለም መንግስታት ኣውግዘውታል።
በኣገራችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት በከባድ ያስቀጣሉ።
ለዚሁ ድርጊት በተጋለጡት ሴቶች ላይ ስቃይና ችግር የሚያስከትል ልምድ ስለሆኔ፡ ለልጆቻችሁ ደሕንነት ሲባል ለዘላለሙ መወገድ ኣለበት።
የጤናና የቤተሰብ መምርያ ኣካሎች እንዲሁም የስደተኛ ሴቶች ማሕበር፡ በዚሁ ጉዳይ ለይ ምክርና ድጋፍ እንዲሰጡዋችሁ ዝግጁ ናቸው።
ስለዚህ ተጨማሪ ድጋፍና መረጃ ካስፈለጋችሁ በኣካባቢያችሁ የሚገኙትን የጤና ክፍሎች ወይንም በቤተሰብ መምርያ ማዕከሎች ጎራ እንድትሉ እንጋብዛቹሃለን።
ለተጨማሪ መረጃ የእኩል ዕድሎች ሚኒስቴር የመረጃ መርበብ መጎበኘት ትችላላችሁ። www.pariopportunita.gov.it







የድሬስ ኣሮ ሑርሲ መጋን
እንዲሁም የፕሮፌሶር ክላውዲዮ ጊዮራልዲኖ
እንዲሁም የውጭ ማሕበሬሰቦች ሸንጎ ትብብር
ሳይንሳዊ ኣስተዋጽኦ ምስጋና የገባዋል ብለዋል

ሓሳቡ ያመንጨት

# የምኒስቴሮች ምክር ቤት ፕርሲደንሲ
# የአኩል ዕድሎች ምኒስቴር

www.pariopportunita.gov.it

## በመተባባር

የጤና ምኒስቴር

የውጪ ጉዳይ ምኒስቴር

የኣገር ውስጥ ጉዳይ ምኒስቴር

የትምህርት ምኒስቴር፤
ዩኒቨ̈ርስቲና ምርምር

የምኒስቴሮች ምክር ቤት ፕረሲደንሲ
ቀዋሚ ኮንፈረንስ ለዝምድና በመንግስት፤
በዞኖችና፤ በነጻዎቹ የትረንቶና
የቦልዛኖ ጠቅላይ ግዛቶች መሃከል።

የስራና ማሕበራዊ
ፖሊሲዎች ምኒስቴር